በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣
ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር

# የበልግ ወቅት አጋማሽ የአየር ጠባይ ግምገማና እና ትንበያ መጽሔት

## እ.ኤ.አ ከፌብሪዋሪ 1 እስከ ማርች 31/2024 የነበረው የአየር ጠባይ ግምገማና ያሳደረዉ ተፅዕኖ

## እንዲሁም ከኤፕሪል 1 እስከ ሜይ 31/2024 የሚኖረው የአየር ጠባይ ትንበያ እና ምክረ ሃሳብ

ኤፕሪል 2024
አዲስ አበባ

ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

ርዕስ ገፅ

**ምዕራፍ አንድ** - 2 -

ካርታ፡1ሀ እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 1 እስከ ማርች 31/2024 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ - 6 -

ካርታ፡1ለ እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 1 እስከ ከማርች 31/2024 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት ብዛት - 6 -

ካርታ፡ 1ሐ እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 1 እስከ ከማርች 31/2024 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር - 7 -

**ምዕራፍ ሁለት** - 8 -

2.1 **እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 1 እስከ ሜይ 31/2024 የሚኖረው** - 8 -

**የአየር ጠባይ አዝማሚያ** - 8 -

**ምዕራፍ ሶስት** - 9 -

**3.1 እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 1 እስከ ማርች 31/2024 የነበረው የአየር ጠባይ በግብርና ስራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ** - 9 -

**3.2 እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 1 እስከ ማርች 31/2024 የነበረው የአየር ጠባይ በዉሀዉ ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ** - 11 -

**3.3 እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 1 እስከ ማርች 31/2024 የነበረው የአየር ጠባይ በጤናው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ** - 11 -

ካርታ 12 እ.ኤ.አ ከማርች 1 እስከ 31/2024 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር - 13 -

**ምዕራፍ አራት** - 13 -

**4.1 እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 1 እስከ ሜይ 31/2024 የሚኖረው የአየር ጠባይ በግብርናው እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ** - 13 -

**4.2 እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 1 እስከ ሜይ 31/2024 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ** - 14 -

**4.3 እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 1 እስከ ሜይ 31/2024 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በጤናው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ** - 15 -



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብሳይት www.ethiomet.gov.et

## በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣ ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር

## እ.ኤ.አ ከፌብሪዋሪ 1 እስከ ማርች 31/2024 የነበረው የአየር ጠባይ ግምገማና በቀሪዎቹ የበልግ ወራት የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ

# አጠቃላይ

በመደበኛ ሁኔታ የበልግ ወቅት ለሀገሪቱ ደቡባዊ አጋማሽ አካባቢዎች ዋነኛ የዝናብ ወቅታቸዉ ሲሆን፤ ለሰሜን ምስራቅ፣ ለመካከለኛዉ፣ ለምስራቅ፣ ለደቡብ ደጋማ አከባቢዎች እና ለደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል አካባቢዎች ሁለተኛ የዝናብ ጊዜያቸዉ በመሆኑ ለአርብቶ አደሩና ለግብርና ስራ እንቅስቃሴ ከፍተኛ አስተዋጽዖ አለዉ፡፡ የወቅቱ የዝናብ አጀማመር፣ መጠንና ስርጭት መስተካከል ለመጠጥ ዉሃ፣ ለእንስሳት መኖ፣ ለእርሻዉ እና ለቆላማ አካባቢዎች የከባቢዉን የአየር ሙቀት ከማርገብ አንፃር ጉልህ አስተዋፅኦ አለዉ፡፡ በዚህ ጽሁፍ ያለፈዉ የበልግ ሁለት ወራት የአየር ጠባይ ግምገማና የቀጣዩ ሁለት ወራት አዝማሚያን ግንዛቤ የሚሰጥበት ይሆናል፡፡

የዘንድሮው በልግ የአየር ጠባይ ትንበያ በተሰጠበት ወቅት የትሮፒካል ፓስፊክ ምስራቃዊና መካከለኛዉ ክፍሎች የባህር ወለል ሙቀት ከመደበኛው በላይ መሞቅ ሁኔታ በበልግ ወራትም ከመደበኛው በላይ የመሞቅ (ENSO- El Nino) ሆኖ የመቀጠል እድሉ 84 % ሊሆን እንደሚችል ግንዛቤ ተወስዶ ነበር፡፡ በተጨማሪም የደቡባዊ እና ደቡብ ምስራቅ የህንድ ዉቅያኖስ ክፍል የባህር ወለል ሙቀት ከመደበኛው መሞቅ ጋር ተያይዞ የዘንድሮ የበልግ ወቅት (Neutral-IOD) ተፅእኖ ሥር ሊሆን እንደሚችል የትንበያ መረጃዎች አመላክተዋል፡፡ በመሆኑም ከአረብ በህር ወደ ሀገራችን ሊገባ የሚችለዉ እርጥበት አዘል አየር በልግ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት አከባቢዎች ላይ አዎንታዊ ተፅዕኖ ሊኖረው እንደሚችል መጠቆሙ ይታወሳል። በመሆኑም በልግ ዋነኛ የዝናብ ወቅታቸዉ የሆኑት የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ከመደበኛው በላይ ዝናብ እንዲኖር ሊያደርግ እንደሚችል ትንበያ ተሰጥቷል። በዚህ መሰረት ባለፉት ሁለት ወራት በልግ ዋነኛ የዝናብ ወቅታቸዉ የሆኑት የደቡብ እና ደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች በብዙ ቦታዎቻቸዉ ላይ መደበኛና ከመደበኛ በላይ ዝናብ አግኝተዋል፡፡ በተጨማሪም ባለፉት ሁለት የበልግ ወራት ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸዉ የሆኑት የሰሜን ምስራቅ፣ የመካከለኛዉ፣ የምስራቅ እና የደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ አካባቢዎች በብዙ ቦታዎቻቸዉ ላይ መደበኛና ከመደበኛ በላይ የዝናብ መጠን ተመዝግቧል፡፡



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

በዚህ ጽሁፍ ውስጥ ባለፉት ሁለት የበልግ ወራት የነበረው የአየር ጠባይ ግምገማና በቀሪዎቹ ወራት ሊኖር የሚችለው የአየር ጠባይ አዝማሚያ እንዲሁም በግብርናው፣ በዉሃ ሴክተሮች እና በጤና ላይ አሳድሮ የነበረው ዳሰሳ እንዲሁም ወደፊትም ሊፈጥር በሚችለው ተፅእኖ ላይ ጽሁፍ ይቀርባል።

# ምዕራፍ አንድ

## 1.1 እ.ኤ.አ ከፌብሪዋሪ 1 እስከ ማርች 31/2024 የነበረው የአየር ጠባይ ግምገማ

ባለፉት ሁለት የበልግ ወራት (ከፌብሪዋሪ እስከ ማርች) 2024 በአብዛኛዉ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የዝናቡ መጠን እና ስርጭት ቀስ በቀስ እየተስፋፋ እና እየተጠናከረ የመጣበት ሁኔታ የነበር ሲሆን፤ በተለይም በፌብርዋሪ ወር በደቡብ፣ በደቡብ ምዕራብ፣ በመካከለኛዉ እና በሰሜን ምስራቅ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ ከዕለት ወደ ዕለት የደመና ሽፋን እና ክምችት ተጠናክሮ ተስተውሏል፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ በደቡብ ምዕራብ፣ በመካከለኛዉ፣ በሰሜን ምስራቅ እና በምዕራብ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ በተጨማሪም በማርች የመጀመሪዉ አስር ቀናት እና የሶስተኛው አስራ አንድ ቀናት ከተጠናከሩት የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በመነሳት ዕርጥበታማው አየር ከህንድ ዉቅያኖስ ወደ ሀገራችን እንዲገባና በተለይም በምስራቅ አጋማሽ እና በምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች በብዙ ስፍራዎቻቸዉ ላይ የነበረዉ ጠንካራ እና የተሻለ የደመና ክምችት ጋር ተያይዞ በምስራቅ፣ በደቡብ ምስራቅ፣ በመካከለኛዉ፣ በደቡበ ምዕራብ እንዲሁም በሰሜን ምስራቅ የሀገሪቱ አከባቢዎች በብዙ ቦታዎቻቸዉ ላይ ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ ከተመዘገበባቸዉ ስፍራዎች መካከል በአዲስ አበባ ቦሌ 56.2 እና 30.5፣ በአዲስ አበባ ጥቁር አንበሳ 32.3፣ በቢሾፍቱ 30.0፣ 30.2 እና 55.4፣ በድሬ ዳዋ 52.1፣ በጎሬ 39.8፣ በጅማ 37.1፣ በመተሃራ 68.8፣ 34.8 እና 68.6፣ በባሌ ሮቤ 30.4፣ በግዮን 31.4፣ በጋቲራ 35.6፣ 38.6፣ በቁሉምሳ 49.7፣ 30.2 እና 44.5፣ በሊሙገነት 40.0 እና 44.7፣ በማጂ 70.5፣ 50.1፣ በማሻ 57.2፣ 30.2፣ 30.6፣ 34.6፣ 30.0 እና 70.6፣



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢ.ሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብሳይት www.ethiomet.gov.et

በሳዉላ 30.8፣ በሲርንቃ 49.4፣ በአቦምሳ 36.6፣ 96.0 እና 31.7፣ በአዳማ 54.1፣ በቴፒ 35.0፣ በአማን 32.5፣ በአምቦ 31.7፣ በአምደ ወርቅ 34.0፣ በአዋሽ አርባ 34.0፣ በባቲ 32.0፣ በበደሌ 70.7 እና 42.7፣ በቦሬ 30.3 እና 36.2፣ በቡኢ 31.6፣ 33.5፣ 43.3፣ 51.0፣ 30.3 እና 36.2፣ በቡሬ 34.4፣ 39.3 እና 30.0፣ በቡርጂ 54.0፣ በጭፍራ 52.2፣ በጭራ 59.5፣ በዳሊፋጊ 35.4 እና 52.2፣ በደብረ ወርቅ 30.9፣ በዶሎመና 30.7 እና 80.0፣ እንዋሪ 41.8፣ በፍቼ 32.4፣ በገለምሶ 87.0፣ በጊኒር 30.0፣ በሀረር 41.7 እና 30.0፤ በሆሳዕና 42.0፤ በኮንሶ 33.5፤ በሜኤሶ 40.7፣ በማይጨው 31.5፤ በማጀቴ 44.1 እና 57.2፣ በማጂ 46.5፣ በኑራኤራ 72.6፣ በስንቃጣ 31.9፣ በተርጫ 48.9፣ በወራቤ 70.6 እና 30.1፣ በያቤሎ 34.5፣ በባቱ 71.5፣ በዉጫሌ 48.0፤ በቂሉቢ 46.1፣ በሂርና 48.1 እና 76.0፣ በግራዋ 40.0፣ በኩርፋ ጨሌ 30.5፣ በቀብሪ በያ 38.5፣ በጨለንቆ 41.7 እንዲሁም በሞያሌ 24.3 በሚ.ሜ ይገኙበታል፡፡

በተጨማሪም ባለፉት ሁለት የበልግ ወራት ከተመዘገበው የዝናብ መጠን የበለጠ ተመዝግቧል፡፡ ከተመዘገበባቸዉ የሚቲዎሮሎጂ ጣቢያዎች መካከል በአዲስ አበባ ቦሌ 56.2፣ በጋቲራ 38.2፣ በማሻ 57.2፣ በመሃል ሜዳ 29.0፣ በአቦምሳ 96.0፣ በቡርጂ 54.0፣ በጭፍራ 52.2፣ በጭራ 59.5፣ በቢሾፍቱ 55.4፣ በገለምሶ 87.0፣ በሂርና 76.0፣ በማሻ 70.6፣ በመተሃራ 68.6፣ በዶሎመና 80.0 እንዲሁም በዊጫሌ 48.0 በሚ.ሜ ይገኙበታል፡፡

ባለፈዉ የበልግ ወቅት አጋማሽ (ከፌብሪዋሪ እስከ ማርች) 2024 የዘነበው የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ ቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም ከኦሮሚያ ክልል ቦረና፣ ባሌ፣ አርሲ እና ምዕራብ አርሲ፣ ምዕራብ ሀረርጌ፣ ሁሉም የሸዋ ዞኖች፣ ሆሮ ጉዱሩ ወለጋ፣ ቡኖ በደሌ፣ ኢሉባቦር፤ ከአማራ ክልል ደቡብ ወሎ፣ ደቡብ ጎንደር፣ የኦሮሚያ ልዩ ዞን፣ ሰሜን ሸዋ፤ ከአፋር ክልል ዞን 4፣ 5 እና 3፤ ሁሉም የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል፤ የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል፤ የሲዳማ ክልል እና የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች ላይ ከ131-468 ሚ.ሜ የሚደርስ ከ15-31 ቀናት ያህል ዝናብ የነበራቸዉ ሲሆን፤ ከቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል የመተከል፣ የአሶሳ፣ የካማሺ እና የማኦ ኮሞ ልዩ ዞን፤ ከጋምቤላ ክልል የአኝዋክ፣ የኑዌር እና የኢታንግ ልዩ ዞን፤ ከትግራይ ክልል ምስራቅ፣ ማዕከላዊ፣ ሰሜን ምዕራብ፣ ደቡብ ምስራቅ እና ምዕራብ ዞኖች፤ ከአፋር ክልል ዞን 2 እና 1፤ ከአማራ ክልል ሰሜን፣ ማዕከላዊ እና ምዕራብ ጎንደር፣ ምስራቅ እና ምዕራብ ጎጃም፣ አዊ ዞን እንዲሁም ከሱማሌ ክልል ፋፋን፣ ጀረር፣ ኤረር፣ ኖጎብ፣ ቆራሄ፣



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢ.ሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብሳይት www.ethiomet.gov.et


ሸበሌ፣ አፍዴር፣ ሊበን እና ዳዋ ዞኖች ላይ ከ20-130 በሚ.ሜ የሚደርስ ከ1-9 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 1ሀ እና 1ለ)፡፡


ባለፈዉ የበልግ ወቅት አጋማሽ (ከፌብሪዋሪ እስከ ማርች) 2024 የዘነበው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር ሲነፃፀር ሁሉም የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል፤ የሲዳማ ክልል፤ የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል እና የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች፤ ከጋምቤላ ክልል የኢታንግ ልዩ ዞን፣ ኑዌር እና ማዦንግ ዞኖች፤ ከቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል አሶሳ፣ ካማሺ እና ማኦ ኮሞ ዞኖች፤ ሁሉም የሱማሌ ክልል ዞኖች፤ ከአማራ ክልል ሰሜን፣ ማዕከላዊ፣ ደቡብ እና ምዕራብ ጎንደር፣ ሰሜን እና ደቡብ ወሎ፣ ዋህግምራ፣ የኦሮሚያ ልዩ ዞን፣ ሰሜን ሸዋ፣ አዊ ዞን፣ ምስራቅ እና ምዕራብ ጎጃም፤ ከአፋር ክልል ዞን 2፣ 4፤ 5 እና 3 እንዲሁም አዲስ አበባ፣ ድሬዳዋ ሀረሪ እና ላይ መደበኛ እና ከመደበኛ በላይ የዝናብ መጠን ነበራቸዉ (ካርታ 1ሐ)፡፡

በአጠቃላይ የበልግ ወቅት አጋማሽ ማለትም ከፌብርዋሪ እስከ ማርች ወራት የዘነበው የዝናብ መጠን በደቡብ እና በደቡብ ምዕራብ፤ በመካከለኛዉ እንዲሁም በሰሜን ምስራቅ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ የተስፋፋ ዝናብ እንደነበረና በመጠን ረገድም ከ131-468 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ እንደተመዘገበ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ በሁለቱ ወራት ከሚጠበቀዉ መደበኛው የዝናብ መጠን ጋር ሲነጻጸር በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል፤ በደቡብ ኢትዮጵያ ክልል፤ በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል፤ በሱማሌ ክልል፤ በጋምቤላ ክልል እና በቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል እንዲሁም በትግራይ ክልል ዞኖች ላይ መደበኛና ከመደበኛው በላይ ዝናብ ተስተውሏል (ካርታ 1፣2 እና 3)፡፡፡ በሌላ በኩል በተለይም በሀገሪቱ ቆላማ አካባቢዎች ማለትም በምስራቅ፣ በደቡብ ምስራቅ፣ በምዕራብ እና በሰሜን ምዕራብ አከባቢዎች ላይ የቀኑ ከፍተኛ የሙቀት መጠን በአብዛኛዎቹ ቀናቶች ከ35 ዲ.ሴ በላይ ሆኖ መቆየቱ ተስተዉሏል፡፡




ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብሳይት www.ethiomet.gov.et











ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብሳይት www.ethiomet.gov.et




ካርታ፡1ሀ  ኢ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 1 እስከ ማርች 31/2024 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ




ካርታ፡1ለ ኢ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 1 እስከ ከማርች 31/2024 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት ብዛት




ካርታ፡ 1ሐ እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 1 እስከ ከማርች 31/2024 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብሳይት www.ethiomet.gov.et

## ምዕራፍ ሁለት

### 2.1 እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 1 እስከ ሜይ 31/2024 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ

በመደበኛ ሁኔታ በኤፕሪል ወር የበልግ ወቅት የዝናብ ሥርጭትና መጠን በተለይም በበልግ አብቃይ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ እየተጠናከረና እየተስፋፋ የሚሄድበት ጊዜ ከመሆኑ አንፃር ከተቀሩት የበልግ ወራት አማካይ ዓመታዊ መጠን የተሻለ ድርሻ አለው። በሜይ ወር ደግሞ የዝናቡ ሥርጭት ከደቡብና ደቡብ ምሥራቅ ኢትዮጵያ አካባቢዎች ቀስ በቀስ እየቀነሰ የሚሄድ ሲሆን፤ በአንጻሩ ደግሞ በምዕራብና በሰሜን ምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ እየተስፋፋ ይሄዳል።

በመጪዎቹ ሁለት ወራት (ኤፕሪል እና ሜይ) አሁን በመታየት ላይ ያለው የትሮፒካል ፓስፊክ ውቅያኖስ የባህር ወለል በኤፕሪል ወር ከመደበኛው በላይ መሞቅ (El Nino) ክስተት ተጽዕኖ ሥር ሆኖ እንደሚቀጥል እንዲሁም በሜይ ወር የባህር ወለል ሙቀት እየቀነሰ እንደሚሄድና ከመደበኛ ጋር በተቀራረበ መቀዝቀዝ (ENSO- neutral) እስከ የክረምት ወቅት መግቢያ ወር ድረስ እንደሚቀጥል የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ። በተጨማሪም በሰሜናዊ ህንድ ውቅያኖስ የነበረው ከመደበኛ ጋር ተቀራራቢ የሆነ የባህር ወለል ሙቀት (Near neutral- IOD) ሁኔታ እንደሚያሳይ የትንበያ መረጃዎች ያመላክታሉ።

ስለሆነም በኤፕሪል ወር ዝናብ ሰጪ የሚቲዎሮሎጂ ክስተቶች አንፃራዊ ጥንካሬ እንደሚኖራቸው ይጠበቃል። ከዚሁ ጋር ተያይዞ በበልግ ዝናብ ተጠቃሚ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ካለፉት ወራት በተሻለ ሁኔታ ዝናብ እንደሚኖር የትንበያ መረጃዎች ያመለክታሉ። በዚህም መሠረት ጋምቤላ፤ ኦሮሚያ፤ የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ፤ የደቡብ ኢትዮጵያ፤ የማዕከላዊ ኢትዮጵያ፤ የሲዳማ ክልል፤ አዲስ አበባ፤ የሶማሌ ክልል እንዲሁም ድሬዳዋና ሀረሪ አካባቢዎች መደበኛና ከመደበኛ በላይ ዝናብ ይኖራቸዋል፡፡ በተጨማሪም የአፋር፤ የምስራቅና የደቡብ ትግራይ፤ በአማራ አካባቢዎች ላይ የዝናቡ መጠንና ሥርጭት እየተስፋፋ የሚሄድ በመሆኑ፤ መደበኛ ዝናብ ያገኛሉ፡፡



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢ.ሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብሳይት www.ethiomet.gov.et

በሜይ ወርም በልግ ዋናኛና ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ ቀጣይነት እንደሚኖረው ይጠበቃል፡፡በዚህም መሠረት በመጪው ሜይ የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ፤ የደቡብ ኢትዮጵያ፤ የማዕከላዊ ኢትዮጵያ፤ የሲዳማ ክልል፤ የጋምቤላና የቤንሻንጉል ክልል መደበኛና ከመደበኛው በላይ ዝናብ ይኖራቸዋል፡፡ የምዕራብና መካከለኛው ኦሮሚያ እና ምዕራብ አማራ መደበኛ ዝናብ እንደሚያገኙ ይጠበቃል።

በአጠቃላይ በመጪዎቹ ሁለት ወራት በአብዛኛዎቹ የበልግ አብቃይ አካባቢዎች ላይ ወቅታዊው ዝናብ ቀጣይነት እንደሚኖረው የሚጠበቅ ሲሆን፤ በተለይም በኤፕሪል ወር በአብዛኛዎቹ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተሻለ የዝናብ ሁኔታ እንደሚኖርና በጥቂት ስፍራዎች ላይም ቅጽበታዊ ጎርፍ ሊያስከትል የሚችል ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ይኖራል፡፡ በሌላ በኩል በሜይ ወር ከክረምት ዝናብ መጀመር ጋር ተያይዞ በምዕራባዊው የሀገሪቱ አጋማሽ ላይ የተሻለ የዝናብ መጠንና ስርጭት ሊኖራቸው እንደሚችል ይጠበቃል።

## ምዕራፍ ሶስት

### 3.1 እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 1 እስከ ማርች 31/2024 የነበረው የአየር ጠባይ በግብርና ስራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ


ባለፉት ሁለት የበልግ አጋማሽ ወራት በተለይም በፌብሪዋሪ ወር በመጀመሪያው እና በሁለተኛው አስር ቀናት የተገኘው እርጥበት ከቀላለ እስከ ከባደ መጠን ያለው ሲሆን፤ ይህም ሁኔታ የአፈር ውስጥ እርጥበት እንዲሻሻል ያደረገ እንደነበረ የተተነተኑ የግብርና ሚቲዎሮሎጂ አመላካቾች ያሳያሉ፡፡ በተጨማሪም በማርች ወር የነበነረው የእርጥበት ስርጭት ብዙ የበልግ አካባቢዎችን የሸፈነና የተስፋፋ ነበር። በአጠቃላይ በሁለቱ የበልግ አጋማሽ ወራት የተገኘው እርጥበት የማሳ ዝግጅትን አስቀድሞ ለመጀመርና ሰብሎችን በወቅቱ ለመዝራት እንዲሁም ለቋሚ ተክሎች የውሃ ፍላጎት መሟላት ከፍተኛ ጠቀሜታ የነበረው ሲሆን፤ አስቀድመው ለተዘሩ የበልግ ሰብሎች፣ ለቋሚ ተክሎችም ሆነ ከማርች በኋላ ለሚዘሩ እንደ በቆሎና ማሽላ ለመሳሰሉ የረጅም ጊዜ ሰብሎችን ለመዝራት የተገኘው እርጥበት




ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብሳይት www.ethiomet.gov.et

አዎንታዊ ሚና ነበረው፡፡ በሌላ በኩል የተገኘው እርጥበት በአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች ለመጠጥ ውሃና ለግጦሽ ሣር አቅርቦት መሻሻል የጎላ ጠቀሜታ ነበረዉ (ካርታ 3ሀ እና ለ) ፡፡

በአንዳንድ አካባቢዎች ላይም ከነበረው ከባድ ዝናብ ጋር ተያይዞ የተገኘው ከፍተኛ መጠን ያለው እርጥበት በተለይም ውሃ አጠር ለሆኑት አካባቢዎች የዝናብ ውሃን ለማሰባሰብና ለማከማቸት መልካም አጋጣሚን የፈጠረ ቢሆንም፤ በአንዳንድ ቦታዎቻቸው ላይ ቅጽበታዊ ጎርፍና የወንዞች መሙላት ሊያስከትል በመቻሉ በእንሰሳት፣ በሰዎችና በንብረት ላይ እንዲሁም ቀደም ብለው በተዘሩና በተለያየ የእድገት ደረጃ ላይ በሚገኙት ሰብሎች ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ነበረው፡፡



ካርታ 3ሀ እ.ኤ.አ ፌብርዋሪ 2024 የእርጥበት ደረጃ ጠቋሚ





ካርታ 3ለ እ.ኤ.አ ማርች 2024 የእርጥበት ደረጃ ጠቋሚ



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብሳይት www.ethiomet.gov.et

## 3.2 እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 1 እስከ ማርች 31/2024 የነበረው የአየር ጠባይ በዉሀዉ ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባለፉት ሁለት የበልግ ወራት በኦሞ ጊቤ፣ ስምጥ ሸለቆ፣ የላይኛውና የመካከለኛው ባሮ አኮቦ፣ የአባይ ደቡባዊ ክፍል፣ በጥቂት የላይኛው ዋቤ ሸበሌ እና ገናሌ ዳዋ እንዲሁም የላይኛው እና ጥቂት የመካከለኛው አዋሽ ተፋሰሰች ከቀላል ከመጠነኛ እስከ ከፍተኛ እርጥበት አግኝተዋል (ካርታ 3 ሐ እና መ) ።




ካርታ 3ሐ ፌብርዋሪ 2024

ካርታ 3መ ማርች 2024


## 3.3 እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 1 እስከ ማርች 31/2024 የነበረው የአየር ጠባይ በጤናው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

የመጀመሪያው የበልግ 2024 የፌብርዋሪ ወር ላይ ለወባ በሽታ መፈጠርና መስፋፊት ምቹ የነበሩ የሀገሪቱ አካባቢዎች አብዛኛው የምዕራብና የደቡብ ኦሮሚያ ቦታዎች፤ አብዛኛው የአፋር ክልል፤  የጋምቤላ ምሥራቃዊው ክልል፤ የደቡብ እና የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል፤ የሲዳማ ክልል እና ጥቂት የምሥራቅ አማራ አዋሳኝ ቦታዎች ላይ ለወባ መፈጠር በዝቅተኛ ደረጃ ምቹ የአየር ሁኔታ እንደነበረ የተተነተኑት የጤና ሚቲዎሮሎጅ መረጃዎች



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብሳይት www.ethiomet.gov.et

ያሳያሉ (ካርታ 3ሰ)። እንዲሁም በማርች 2024 ወር የነበረውን የአየር ጠባይ ለወባ በሽታ መፈጠርና መስፋፋት ምቹ የነበሩ የሀገሪቱ አካባቢዎች በስርጭትም ሆነ በመጠን ከፌብርዋሪ ወር የተጠናከረ ሲሆን፣ በዚህም አብዛኛው የምዕራብ ኦሮሚያ ክልል፣ ደቡብ ምዕራብና የደቡብ ኢትዮጵያ ህዝቦች ክልል፣ የመካከለኛው ኢትዮጵያና የሲዳማ ክልል፣ አብዛኛው የጋምቤላ ክልል፣ ደቡባዊ የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል እና አብዛኛው የአፋርና ጥቂት የምሥራቅ አማራ አዋሳኝ ቦታዎች ከዝቅተኛ እስከ መካከለኛ ምቹ የሆነ የአየር ሁኔታ ነበራቸው (ካርታ 3ሸ)።





ካርታ 3ሡ. ፌብርዋሪ 2024


ካርታ 3ረ ማርች 2024


በሌላ በኩል በበልግ 2024 የነበረውን የአየር ሁኔታ በሰው ልጅ የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረውን ተጽዕኖ ስንመለከት በፌብርዋሪ እና በማርች ሁለት የበልግ ወራት ላይ አብዛኛው የሀገሪቱ ክፍል ላይ ለሰዎች ተስማሚ የሆነ የአየር ሁኔታ ነበራቸው፡፡ በሌላ በኩል በአንዳንድ የአፋርና የጋምቤላ እንዲሁም በጥቂት የሶማሌ ደቡባዊ ዝቅተኛ ቦታዎች እና የምዕራብ አማራ ዝቅተኛ ቦታዎች ላይ ከፍተኛ ጥንካሬ የነበረውና ምቹ ያልሆነ የአየር ሁኔታ እንደነበረ የተሰበሰቡና የተተነተኑ የጤና ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያሳያሉ (ካርታ 2 ሀ እና ለ) ፡፡



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብሳይት www.ethiomet.gov.et





ካርታ 3ሰ ፌብርዋሪ 2024

ካርታ 3ሸ. ማርች 2024

## ምዕራፍ አራት

### 4.1 እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 1 እስከ ሜይ 31/2024 የሚኖረው የአየር ጠባይ በግብርናው እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በመጪው የኤፕሪል ወር በመጠንም ሆነ በሥርጭት የተሻለ እርጥበታማ ሁኔታ (Moist condition) የሚኖር ሲሆን፤ በሜይ ወር ደግሞ በተለይም በምዕራብና በደቡብ ምዕራብ ክፍሎች ላይ የተጠናከረ እርጥበት ሊኖር እንደሚችል ይጠበቃል፡፡ ይህም ሁኔታ የበልግ

አብቃይ እና ተጠቃሚ አካባቢዎች ለሚያከናውኑት የግብርና እንቅስቃሴ አመቺ ሁኔታን የሚፈጥር ሲሆን ቀደም ብለው ለተዘሩና በቡቃያና በተለያየ የእድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ የበልግ ሰብሎችና ለቋሚ ተክሎች የውሃ ፍላጎት መሟላት ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል፡፡ በተጨማሪም በደቡብና ደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች ለሚዘሩ ሰብሎችም ሆነ በአርብቶ አደር አካባቢዎች ለእንስሳት የግጦሽና የመጠጥ ውሃ አቅርቦት ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡ በተጨማሪም በተለያየ ምክንያቶች የበልግ ወቅት የእርሻ እንቅስቃሴን ዘግይተው ለጀመሩና የረጅም ጊዜ ሰብሎችን ለመዝራት የሚጠበቀው እርጥበት አመቺ ሁኔታን እንደሚፈጥር ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ከወዲሁ ዝግጅት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ በሌላ በኩል በአንዳንድ የሀገሪቱ አካባቢዎች በጣም እርጥበታማ ሁኔታ ሊፈጠር ስለሚችል በተለይም ውሃ ገብና የአፈር ጠባያቸው በቀላሉ ውሃን በማያሰርግባቸው አካባቢዎች ባሉ ማሳዎች ላይ የአፈር ውስጥ እርጥበት መብዛትን ሊያስከትልና በማሳዎች ላይ ውሃ እንዲተኛ ሊያደርግ ስለሚችል ተገቢው ትኩረት ተደርጎ የበዛውን ውሃ በቀላሉ ለማጠንፈፍና ለማስወገድ የሚያስችሉ ዘዴዎችን ከወዲሁ መተግበር ያስፈልጋል፡፡

## 4.2 እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 1 እስከ ሜይ 31/2024 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በኤፕሪል ወር በኦሞጊቤ፣ ስምጥሸለቆ፣ የላይኛውና የመካከለኛው አዋሽ፣ አባይ፣ ገናሌዳዋ፣ የላይኛው እና የመካከለኛው ተከዜ፣ ዋቤ ሸበሌ፣ እንዲሁም አፋር ደናከል ተፋሰሶች ላይ ከመጠነኛ እርጥበት እስከ ከፍተኛ እርጥበት እንደሚያገኙ ይጠበቃል፡፡ በሜይ ወር በአብዛኛው ባሮ አኮቦ፣ ገናሌ ዳዋ፣ ዋቤ ሸበሌ፣ ኦሞ ጊቤ፣ ስምጥ ሸለቆ፣ በመካከለኛው እና በታችኛው አባይ እና በላይኛው አዋሽ ተፋሰሶች ላይ ከመጠነኛ እርጥበት እስከ ከፍተኛ እርጥበት እንደሚኖረው የትንበያ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ በአንጻሩ ግን አልፎ አልፎ ሊኖር ከሚችለው ከባድ ዝናብ ጋር ተያይዞ በተለይም በከተሞች አካባቢና ለጎርፍ ተጋላጭ በሆኑ ተፋሰሶች እና ንዑስ ተፋሰሶች ላይ ቅጽበታዊ ጎርፍም ሆነ የወንዞች ሙላት በማስከተል በንብረትና በሰው ህይወት ላይ ጉዳት እንዳያደርስ አስፈላጊውን የጥንቃቄ ዝግጅት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብሳይት www.ethiomet.gov.et

## 4.3 እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 1 እስከ ሜይ 31/2024 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በጤናው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በኤፕሪል እና በሜይ ወራት ለወባ በሽታ መስፋፋት ምቹ የሆነ የአየር ሁኔታ በጥቂት የኦሮሚያ ክልል፣ የደቡብና ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል፣ የመካከለኛው ኢትዮጵያና የሲዳማ ክልል፣ የምዕራብ አማራ ዝቅተኛ ቦታዎች፣ የቤንሻንጉል እና የጋምቤላ ክልል የወባ ትንኝ እንዲፈጠር የሚያስችል ምቹ የአየር ሁኔታ እንደሚኖር የትንበያ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ ስለሆነም ለወባ ተጋላጭ በሆኑ አካባቢዎች የሚኖሩ የህብረተሰብ ክፍሎች ለወባ መራቢያነት የሚያገለግሉ ምቹ ሁኔታዎችን የማስወገድና የማጽዳት ተግባራት በትኩረት ማናወን ያስፈልጋል፡፡



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብሳይት www.ethiomet.gov.et